Ephi Lata:

ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት፤ መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ። መዝ

132፡14

ቶ ቶ ቶ ቶ ቶ ቶ ቶ

የ"ቶ" # ፊደል_ቅርፀ_መስቀል_ምስጢር

ቶ ቶ ቶ ቶ ቶ ቶ ቶ

የዚህን ፊደል ትርጉም የትየለሌ ፀሐፍያን የከርሰ ምድር ታሪክ መዝባሪዎች

ምሁራን ቢመራመሩት እስከ አሁን ድረስ ግራ ቢገባቸው "The lost image of

cross" እስከ አሁን የጠፋው ታላቅ ሀይል ያለው የመስቀል ምልክት በሚል ፅሁፍ

አበርክተዋል። እጅግ ምስጢራዊነቱ የሚነገርለት የተፃፈለት ይህ በ "ቶ" ፊደል

ስለተቀረፀው መስቀል ካነበብኩት በጥቂቱ ልበል..........

+

“ቶ  ሠባተኛዋ ፊደል ነች። ሠባት ቁጥር ትልቅ ትርጉም ያላት ነች ፍፁምነትን

የምታመለክት ነች። ሠባተኛው ዙፋን የጌታ እንደሆነ፣ ሠባተኛው ቀን ሠንበት

እንደሆነች፣ 7 ቁጥር ብዙ ሚስጥር አላት።  ቶ  ሠባተኛዋ ቁጥር በመሆኗ

ፍፁምነትን የምታመለክት ነች። ክርስቶስን የምትወክል ነች። ክርስቶስ ለኛ ሲል

በቀራኒዮ መስቀል ላይ ራቁቱን መሠቀሉን የምታመለክት ነች።

+

ትልቁ ከዚህ በላይ ያለው ምስጢር አባቶቻችን ከመፅሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ሲተነትኑ

በሰማይ መላዕክት ዘንድ ውጊያ ሆነ ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ገብርኤል ከሣጥናኤል

ጋር ሲዋጉ ሁለት ጊዜ ተሸንፈዋል። በሶስተኛው እንዲያሸንፉ ሲልካቸው ይህን

ቀስተደመና ቀርፆ፣ ይህን ምልክት የኮከቡን ቅርፅ የ ቶ  ቅርፅ ያለው መስቀል

በየክንፋቸው ቀርፆላቸዋል። "ኤል" የሚለውንም ምስጢራዊ ስም አትሞባቸዋል።

ይህን ካደረገላቸው በኋላ ተመልሰው ወደ ውጊያው ቢሄዱ ሳጥናኤል ሀይላቸውን

ሊቋቋመው አልቻለም ውድቀቱ ፈጠነ ሽንፈቱ የከፋ ሆነበት ፅልመትን አልብሰው

ወደ በርባኖስ ውስጥ ጥልቅ ጨለማ ላይ ወረወሩት። የአምላክ ክንድ ፅኑ መሆኗን

ሳጥናኤል ያውቃልና በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሥላሴን ሥሉስ ቅዱስ እያለ እየተንቀጠቀጠ ይገዛል ይላል። ሆኖም ምግባር ስለሌለው ፅድቅን አያያትም።

+

ሰወች "ቶ"ን የህይወት ምልክት አድርገዉ የሚወስዱት ለኢትዮጵያዉያን ብቻ ነዉ:: የሚገርመዉ ደግሞ ይህ ምልክት አገልግሎት ላይ የዋለዉ ከክርስቶስ ልደት በፊት 3000 አመታት ቀደም ብሎ ጥንት ግብፃዉያን ቶርኔተር (የፑንት ምድር) ብለዉ በሚጠሯት ሀገር ነዉ:: ግብፃዉያን እንደሚሉት የፒራሚድ ግንባታ ጥበብን የተማሩት ከቶርኔተር (የአሁኗ ኢትዮጵያ) ሰወችና አማልክቶች ነዉ::

በ670 አ.አ በኢትዮጵያ ነግሶ የነበረዉ ንጉስ ቲርሀቅ እየሩሳሌም የኦሶር ንጉስ በሆነዉ በሰናክሬም ስትወረር ለእየሩሳሌም መከታ ሆኖ ሲዘምት ሀያላን ከሚባሉ ወታደሮች ጋሻ ላይ የ "ቶ" ምልክት እንደተቀረፀና ንጉሱም በ"ቶ" ቅርፅ የተሰራ መስቀል ማሰሩን የሚያስረዱ የድንጋይ ላይ ፅሁፎች ተገኝተዋል::

የ"ቶ" ምልክት የተፈጠረዉ በቅርብ ግዜ ነዉ ለሚሉ ሰወች "ቶ "የተፈጠረዉ አለም ሲፈጠር ነዉ ብል እዉነት እንጅ ዉሸት አይሆንም:: ለዚህ ማስረጃየ ደግሞ የሰዉ ልጅ የተፈጠረዉ በ"ቶ" ቀመር መሆኑ ነዉ::

ይህ ምልክት ግብፅ በሚገኙ የዋሻ ስእሎች ላይ የህይወትን ገፀ ባህሪ ይዞ እንደነበር የሚያስረዳ ሲሆን ይህ ምልክት አገልግሎት የጀመረዉ ኢትዮጵያ ላይ ከሆነ ግብፅ ላይ እንዴት ተገኘ? ብሎ ለሚጠይቅ ግብፅ ላይ የነገሱት 18 ኢትዮጵያዊ ንጉሶች ተጠቃሽ ናቸዉ::

ሜምኖን የተባለዉ ኢትዮጵያዊ የግብፅ ንጉስ ከ1320 አ.አ እስከ ሴፕዩምስኬኩረስ 170 አ.ም የቆመ ሀዉልት እንደነበረዉና ሀዉልቱም ጠዋት ጠዋት ፀሀይ ሲያርፍበት የክራር ድምፅ ያሰማ እንደነበር ሄሮዱተስ በፓፒረስ ወረቀት ላይ አስፍሮት ይገኛል:: ክራር ደግሞ የኢትዮጵያ የባህል መሳሪያ መሆኑ አጀብ ያስብላል:: በሳባዉያን የዋሻ ላይ ስእሎችና ማህተሞች ላይ "ቶ" ተመስሎ ጣቱን የቀሰረ ምስል እንዳለ (አስቻለዉ ከበደ የተባለ ፀሀፊ ከርከቤዴል ሳዶፍ) በሚል መፅሀፉ አስፍሮታል::

ሳባዉያን ሰዉን ለመሳል "ቶ"ን መጠቀማቸዉ ያጋጣሚ ይመስላችሁአል?

በሮማዉያን አፈ ታሪክ ላይ የህይወት ምልክት ተደርጎ የተወሰደዉ የተጋደመዉ የ ለ ፊደል ሲሆን በግራና በቀኝ ሁለት ጭረቶች አሉት:: ይህ ምልክት ለሮማዉያን ከአማልክቱ የተሰጠ መስሎ ቢታያቸዉም እዉነቱ ግን በአንድ ባልታወቀች የአፍሮዳይት ኦራክል የተፈጠረ እንጅ የህይወት ምልክት ላለመሆኑ ከሰዉ ጋር አብሮ የተፈጠረዉ "ቶ" አስረጅነቱ የት የሌለ ነዉ::

+

ለምሳሌ እንኳ ብንወስድ ጠቢቡ ሰለሞን ታላቁን ቤተመቅደስ ከመስራቱ አስቀድሞ በሚሰራበት ቦታ ላይ አሰድ እሳት የተሰኘችው ኮከብ እና ጸሀይ በ45 ዲግሪ ትይዩ ወጥተው ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ እስራኤል የአንበሳ ከተማ ተብላ ትንቢት ተነግሮላታል አንበሳ አሰድ እሳት የተሰኘው ኮከብ መለያ ምልክት እንደሆነ ልብ ይበሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ወቅት ይህ አሰድ እሳት የተሰኘው ኮከብ ከጸሀይ ጋር ትዩዩ ሆኖ በመውጣት የጌታችን ንጉስነትን አብስሯል፡፡

ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ወቅትም ጸሀይን ጨምሮ የተለያዩ ኮከቦች የመስቀል ቅርጽ ሰርተው በእየሩሳሌም አናት ላይ ታይተዋል፡፡

ምንጭ:- Yunael blog ( ከዩናኤል ቀዩ ንስር)

+++

# ተጨማሪ

# ቶ ጠልሰም[ ምሳሌ፣ አርማና ምልክት] የኢትዮጵያን ምስጢራዊ ታሪክ በማጥናት አለምአቀፍ እውቅና የተሰጣቸው አባ ተስፋሥላሴ ሞገስ ይህን ፅፈዋል:

",,,,, ክርስቶስን የሚወክለው "ቶ" ፊደል የተደረገበት ( በመፅሀፋቸው ላይ በኢትዮጵያ ካርታ መሀል ላይ የ "ቶ"አርማ ይገኛል) ከዓለም ሕዝብ በፊት ጀምሮ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ኦሪትን ከሐዲስ ጋር አዋህዳና አስማምታ የምታምንና የምታሳምን ኢትዮጵያ ብቻ መሆኗን የሚያመለክት ነው, ,,,"

ምንጭ:" ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው የተዋሕዶ አንበሳም

መድኃኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" የተሰኘው የአባ ተስፋ ሥላሴ

ሞገስ መፅሐፍ ።

# ራ

+

" ቶ " እስከዛሬ ከተመለከትነው ትርጉሙ ባሻገርም ሌላ ትርጉም አለው። ቶ አቶ

ወይንም እኔ ማለት ነው። አ፣ ኦ ያሉት ቃላት ከጉሮሮ ተነስተው በአንደበት

የሚሰራጩ አናባቢዎች ናቸው በዚህ መሰረት አ አናባቢ ሲሆን ተነባቢው ቶ ነው።

ከዚህ በመነሳት ቶ ከስም ቀድሞ የሚገባ ባለቤትን አመልካች ነው። ይህ ትርጉም

ከሱባ ቋንቋ ጋር ተዛምዶ እንዳለው መራሪስ አማን በላይ በመፅሃፋቸው ፅፈዋል።

የበለጠ ለማንበብ መፅሃፈ ብሩክ የተሰኘውን መፅሀፍ ገፅ 165 ጀምሮ ያንብቡ።

※ ቶ ※ ቶ ※ ቶ ※ ቶ ※

ቀደምት ሊቃውንት ሁለት ዓይን የተሰጠን በአንዱ የራሳችን በሌላው

የሌላውን ለማየት ነው። ሁለት ጆሮ የተሰጠን በአንዱ የራሳችንን

በሌላው የሌላውን ለመስማት ነው። ሁለት እጅ የተሰጠን በአንዱ

ለመስጠት በሌላው ለመቀበል ነው። ሁለት እግር የተሰጠን በአንዱ

ወደራሳችን በሌላው ወደ ሌላው ለመሄድ ነው ይሉ ነበር።

፳፩ ፳፩ ፳፩ ፳፩ ፳፩

ቤተክርስቲያን ባህረ ጥበባት

አትመረመርም እጅግ ጥልቅ ናት

የሲኦል ደጆች አይችሏትም

ቤተክርስቲያን አትታደስም!

የሐዋርያት ጉባኤ ስለሆነች ስለአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም

እንማልዳለን!

(መጽሐፈ ሚስጢር)

የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን

መላእክት ተራዳኢነት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ የቅዱሳን ሐዋርያት፣

የቅዱሳን አበው መነኮሳት፣ የቅዱሳት አንስት፣ የደናግላንና የቅዱሳን ሁሉ

ምልጃና ቃል-ኪዳናቸው ባለንበት ከሁላችን ጋር ይሁን!!!

✝✝ ✝ ✝ ✝✝

ለአባ ሕርያቆስ ፤

ለቅዱስ ኤፍሬም ፤

ለቅዱስ ያሬድ ፤

ለአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

ለአባ ይስሀቅ

የተገለጸች እመቤታችን እኛንም በበረከት እና በረድኤት ትጎብኘን ፤

ከ